1

ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

የፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሀተታ

ጥር 13 ቀን 2007 ዓ.ም. የተላለፈ

የተነጣጠለ ሕዝባዊ አመፅ ፤

ያልተቀነባበረ ሀገራዊ ትግል

ግቡን አይመታም !

ለዘመናት ሲከማች የቆየው የሀገራችን ችግር፤ መፍተሄው አሁንም እንደ ምድረበዳ ንብልብሊት ( ሚራዥ) የማይጨበጥ እየሆነ መሄዱን ቀጥሏል ። ተከሰተ ሲባል ፤ ይሰወራል። ተጨበጠ ሲባል ያፈተልካል። ተከታትለው ቢይዙትም ያመልጣል። የሀገራችን ችግርና መፍተሄው ሊገጣጠሙ አልቻሉም ። ሰኔና ሰኞ አላገጣጠማቸውም ። መፍተሄውን ፍለጋ የተሰማራውም ሁሉ ፤ ጥረቱና ድካሙ ያተኮረው ፤ በመፍተሄው ፍለጋ ላይ ሳይሆን፤ ገና በችግሩ መኖር አለመኖር ላይ የሚዋትት ይመስላል ። የችግሩን ጥልቀትና ስፋት መረዳቱ ሳይሆን ፤ እንዲያው ከነአካቴው ችግር መኖሩንም የተገነዘበው አይመስልም ። የሀገሪቱን ችግር ካለተረዱ ደግሞ፤ መፈተሄ ፍለጋ መሄድ አይቻልም ። ወይም ደግሞ፤ " ስለችግር መስማት ሰልችቶናልና እባካችሁ አታስቸግሩን፤ ኢትዮጵያ እንደሆነች፤ ዝንተ-ዓለሟን ከችግር የምትወጣ ሀገር አይደለችም " ካልተባለ በስተቀር !

ችግር የለብንም ብሎ መፍተሄ ሳይፈልጉ መቀመጥ፤ ለአምባገነን ሥርዓት አሜን ብሎ እንደ መገዛት ይቆጠራል። በሽታውን ለሀኪም ሳይናገር ደብቆ፤ መዳህኒት ሳያገኙ እየተሰቃዩ ወደ ከርሰ-መቃብር መውረድ ማለት ነው። በሽታቸውን የደበቁ ህሙማንና ችግር አለምኖሩን ያልተረዳ ኅብረተሰብ፤ ለሞትና ለዘለዓለማዊ ባርነት እራሱን አስልፎ እንደሰጠ ይቁጠረው ! ለበሽታው መዳህኒት፤ ለሀገር ችግር ደግሞ መፍተሄ ካልተፈለገ ፤ በህይወት መኖር ትርጉሙን ያጣል። ጤናን ማጣትና ነፃነትን ተገፍፎ መኖር፤ መኖር አይበለው። ይህን የተረዱ ጀግኖች፤እየሞቱ ከመኖር ይልቅ፤ እየሞቱ መኖርን መርጠው የሰዋሉ። በእነርሱ መሞት፤ የሀገርንና የሕዝብን መኖር ይመርጣሉ። በዕርግጥም እየሞቱ ከመኖር ይልቅ፤ እየኖሩ መሞትን የመረጡ ሰማዕታት ናቸው ። ሰማዕታት ደግሞ ብፁዓን ይባላሉ ።

በአሁኑ የሀገራችን የፖለቲካ ሁኔታ ሦስት ኃይሎች ተፋጥጠው ካብ ለካብ ይተያያሉ። ከየአንዳንዳቸው ዕይታ በመነሳት፤ ሦስቱም የየግላቸውን ግንዛቤ ያስተናግዳሉ። እነርሱም ፡-----

1 ኛው የገዥ ፓርቲ ሆኖ፤ አገር የሚገዛው የወያኔ ጉጅለ ነው ።ይህ ቡድን፤ ኢትዮጵያን፤ እንደ ሰም አቅልጨ፤ እንደ ገል ቀጥቅጨ እየገዛኋት ስለሆነ፤ ምንም ችግር በሀገሪቱ ውስጥ የለም ብሎ የሚያምን ነው። ችግር አለ ብለው የሚያወሩ፤ ፀረ

ሠላም፤ ፀረ- ትግሬ የሆኑ፤ ትምክህተኞች ብቻ ናቸው ብሎ፤ ራሱን እየደለለ በምኒልክ ግቢ መሽጎ ተቅምጧል ። በሀገሪቱ ሠላም ሰፍኖ፤ ሕዝብ ተደስቶ፤ ሀብት -ንብርት ተትረፍርፎ፤ ዴሞክራሲ ተስፋፍቶ ሁሉም በልቶ-ጥግቦ ይኖራል ብሎ ራሱን አስምኗል። ወያኔ ከገባ፤ የችግር ምቾት ገደል ገባ አያለ፤ ጓይላ የሚደነክር ብሄረተኛ ስብስብ ነው። በሀገሪቱ ውስጥ አንድችም ችግር የለም ብሎ የደመደመ ይህ የገዥ ቡድን፤ ሁሉንም ተቃዋሚን ሁሉ ፤ ሰጥ-ለጥ አድርጌ መግዛቴን አረጋግጫለሁ ብሎ ራሱን አሳምኗል ። ሠላምን አስፍኛለሁ ብሎ ራሱን እየደለለ፤ የሚቁነጠነጥና በኀልም ወቅያኖስ እየተንሳፈፈ በመጥለቅ ያለ ስብስብ ነው ። ወያኔ አሁን መረጋጋት ሰፍኗል ቢልም፤ ይህ መረጋጋት፤ " ማዕበሉ ከመምጣቱ በፊት የሚከሰት ፀጥታ" መሆኑን ሊገነዘብ አልቻለም

2 ኛው. በተቃዋሚው ጎራ ነኝ የሚለው ክፍል ነው። በዚህ ጎራ የተሰለፉት፤ ራሳቸው፤ በሁለት ረድፍ የተከፈሉ ቡድኖች እንደሆኑ ሕዝቡ ደህና አድርጎ ያውቃል። እነርሱም በብሄር የተደራጁትና በኀብረ-ብሄር አባአላት የተዋቀሩት ድርጅትች ናቸው ።

እነኝህ በሁለት ዓይነት አወቃቀር የተደራጁ ክፍሎች፤ እንደገና ሁለት ዓይነት የተቃውሞ ታርጋ ተሰጥቷቸውል። አንደኛው ህጋዊ ተቃዋሚዎች በሚል ስያሜ ሲታወቁ፤ ሌሎቹ ደግሞ "ህገ- ወጥ" ተቃዋሚዎች የሚል ታርጋ፤ መልያቸው ሆኗል ። ህጋዊ ተቃዋሚዎች የሚባሉት፤ የወያኔን ድርጅታዊ ሰንድንና ህገ አገዛዝን፤ እንደ ሀገራዊ ህገ መንግሥት አምነው- ተቀብለው እያተገዙ " የሚታገሉ " እንደ ሆኑ በሕዝቡ ዘንድ ይታወቃሉ። የብሄር ደርጅቶች፤ ስለ ችግሮቹ አፈረጃጀት ብቻ ሳይሆን፤ ሰለ መፍተሄ አፈላለጋቸውም ጭምር፤ ህገ ወጥ ተቃዋሚዎች ከሚባሉት ጋር ልዩነት አላቸው። በትግል ስልትና በአጀንዳ ቅደም ተከተልም ይለያያሉ። የሀገር ህልውናን አስመልክቶም ተመሳሳይ ራዕይ የላቸውም ።

የኅብረ-ብሄር ድርጅቶች፤ የቅድሚያ አጀንዳቸው የሀገሪቱ ኀልውና፤ የዜጎቿ እኩለነትና የዴሞክራሲ መስፈንና መረጋገጥ እንደሆነ አጽኖኦት ይሰጣሉ። ከማነኛውም በበለጠ፤ የኢትዮጵያን አንድነትና የግዛት ልዕልና መቅደም አለበት ይላሉ። በዚህ መሠረታዊ -ሀገራዊ ልዩነት ምክንያት፤ ከወያኔ ጋር የማይታረቅ ተቃርኖ አላቸው። ከብሄር ድርጅቶችም ጋር ቢሆን የማይታረቅ ልዩነት ላቸው ባይባልም ቅሉ፤ ያለቸው የአቋም ልዩነት በቀላሉ የሚታይ አይደለም ። ይህንን ልዩነት ለማስታረቅ፤ ብዙ ምዕራፍ መጓዝ ሊኖርባቸው እንደሚችል በሕዝቡ በኩል ግንዛቤ አለ ።

የብሄር ድርጅቶች የቅድሚያ አጃንዳቸው የብሄሮቻቸው ነጻነት ነው ባዮች ናቸው። ይህ አቋማቸው ከአገዛዙ ጋር በአንድ ሰፌድ ላይ ያስቀምጣቸዋል ። ህጋዊ ተቃውሚዎች ተብለው የተሰይሙትም በዚህ አቋማቸው ነው።

ባጭሩ፤ ያለውን ሥርዓት ጠጋግኖና ደጋግፎ የጥገና ለውጥ በማደረግ መቅጠል ይቻላል በሚሉት ወገኖችና ፤ ለሀገሪቱ ስር የሰደደ፤ ችግር ዋና ምክንያት የሆነውና ተጠያቂው የወያኔ አገዛዝ ስለሆነ ይህ ሥርዓት መወገድ አለበት በሚለው በኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል የሰማይና ምድር ያህል ርቀት አለ። የዚህ የልዩነት አቋም፤ የሀገሪቱን ችግር በአንድ መነጽር ለማየት የሚያስችል ዕይታን አሳጥቷል ። በተቃዋሚው መካከል፤ የጋራ ችግር መኖሩ ላይ መተማመን እስካልተገኘ ደረስ ፤

የጋራ መፍተሄ መፈለግ የሚቻል አይሆንም ። በሀገራችን የፖለቲካ መድርክ፤ የፖለቲካው ተዋናይ የሆኑ ተጨዋቾች የሚተራመሱትም፤ በሀገሪቱ ችግሮች ላይ የጋራ ግንዛቤና ስምምነት በማጣታቸው ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም።

3 ኛው. የሥርዓቱ ሰላባ ብቻ ሳይሆን፤ የአገዛዙ ተጠቂና የችግሩ ቀጥታ ገፈት- ቀማሽ የሆነው የኢትጵያ ሕዝብ፤ በሦስተኛ ረድፍ በመሆን፤ ተቃዋሚዎቹን እየታዘበ ይገኛል ። የችግሩን ክብደትና መጠን የሚያየውም ከሚኖርበት የዕለት ተዕለት ህይወቱ ጋር በማያያዝ ነው፡፡ ችግሩን መረዳቱ ብቻ ሳይሆን፤ መፍትሄውንም ሳይቀር ያውቀዋል። ጠላቱንና ወዳጁንም በሚገባ ለይቶ መዝግቦታል ። የሀገሪቱን ስር የሰደዱ ችግሮችም የሚመለከትበት መነጽርና የሚለካበት ሚዛን፤ የፖለቲካ ድርጅቶች፤ በሚመለከቱበ መንጽርና በሚለኩበት ሚዛን ጋር በእጅጉ የተለየ ነው። የብሄር ድርጅቶች የሚጠቅሙት ሚዛን፤ ድርብ መለኪያ ( ዳብል ስታንዳርድ ) ነው ለማለት ያስደፍራል ።

ዞሮ ዞሮ፤ በአመዛኙ ፤የፖለቲካ ጥያቄ/ ትግል፤ የመንግሥት ሥልጣን አያያዝ ጉዳይ በመሆኑ፤ ፖለቲከኞች የሀገሪቱን ሁኔታ የሚያዩትና ሊጨነቁበትም የሚፈልጉት ከሥልጣን ጉጉት አኳያ እንደሆነ እነርሱም አይክዱትም ። ይህንን ደግሞ፤የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚገባ ይረደዋል። እስካሁን የተፈራርቁትን ዥዎቹንም ማንነት አበክሮ ያውቀዋል ።

የዐፄው አገዛዝ፤ በስመ መለኮት፤ ደርግ፤ በስመ ሶሻሊዝም፤ ወያኔ ደግሞ በስመ በሄር ነጻ አውጭነት ምን ያህል በሀገርና በሕዝብ ላይ በደል እንደፈጸሙ ያውቀዋል ። እኔ አውቅልሃለሁ በሚለው ፕሮፓጋንዳና አንተ ራስህ ስለ ራስህ አውቀህ የራስክን አስተዳድር መስርትህ ራስህን አስተዳደር፤ በሚለው አዋጅ መከከል ልዩነት እንዳለው፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማንም ሊነግረው አይችልም ። ዴሞክራሲንም ሆነ ነፃነትን በከበሮ ማወጅና በተግባር መተርጎም የተለያዩ በመሆናቸው፤ የዴሞክራሲ ሥርዓት፤ በሀገራችን የውሃ ሽታ እየሆነ ቀርቷል።

ዴሞክራሲ ደግሞ፤ በበጎ ፈቃድና በችሮታ የሚገኝ ሳይሆን፤ በሕዝብ ሙሉ ተሳትፎ፤ በሙብት መረጋገጥ ፤ በህግ የበላይነትና በሕዝብ ልዕልና ነው። ያ ሁሉ ተሟልቷል ቢባልም እንኳ፤ ሥርዓቱ፤ ዋስትናውን ባስተማማኝ ሁኔታ አስረግጦና አሟልቶ አግኝቷል ማለት የሚቻለው የሕዝቡ ሙሉ ተሳትፎ በተግባር ተተርጉሞ፤ ሲረጋገጥ በቻ ነው፡፡ ያን ሥርዓት ለማምጣት፤ በግድ የተባበረ ሕዝባዊ አመፅ ወሳኝ ይሆናል ። የተቀነባበረ ትግል ማራመድ፤ የሀገራችንን ችግር ፈጣሪዎች እንደሚያስወግድ ማመን ያስፈልጋል ።

የተባበረ ሕዝባዊ አመፅን ማንም ኣምባገነነ ሊገታው እንደማይችል፤ የሕዝቦች አመፅ ታሪክ በተደጋጋሚ ያረጋገጠው ዕውነታ ነው። በኛው ሀገርም ይህ ዕውን የማይሆንበት አዳችም ምክንያት ሊኖር አይችልም። ወያኔ፤ ይህ አመፅ እንደሚያጠፋው ደህና አድርጎ ያውቃል። በመሆኑም፤ አመፁ እንዳይቀሰቀስ የተቻለውን ሁሉ መከላከል ያደርጋል ። አመፁ ከተቀሰቀሰም ፤ማነኛውንም ዓይነት የኃይል ርምጃ በመውሰድ፤ ለማዳፈን ይሞክራል። ላለፉት 24 ዓመታት ሲያደርግ የቆየውም ይህንኑ ነበር ።

ቁጥሩ ወደ 90 ሚሊዮን የሚገመተውን ሕዝብ፤ በብሄር ተደራጅተው የመጡ ዕፍኝ የማይሞሉ ቡድኖች "አንቀጥቅጠው " እየገዙና የሀገሪቱም ሀብት ሊዘርፉ የቻሉበት ምሥጢሩ ምንድን ነው የሚለው ጥያቄ እስካሁን አልተጠየቅም ብሎ ለማመን ያስቸግራል ፡፡መልሱም ምሥጢረ- ሥላሴ አይደለም ፡፡ለዓላማቸው መምቻ የሚሆን ድርጅት ፈጥረው፤ ተደራጅተው፤ ታጥቀው፤ የባዕዳኑን ድጋፍ ለማግኘት ሲሉ ፤ ብሄራዊ ክኅደት እስከመፈፀም ደርሰው ነው ፡፡ ይህን መረዳት ደግሞ ከባድ ነበር ብሎ ማለት አይቻልም ፡፡ "ያልተገላበጠ ያርራል " እንደሚባለው ያለተንቀሳቀሰ ሕዝብም ከጭቆና ሊላቀቅ አይችልም፡፡ በግድ ያልተቋረጠ ሕዝባዊ አመፅ መካሄድ ወሳኝነቱ አያከራክርም ፡፡ የአመፅ እንቅስቃሴው የታሰበውን ግብ የሚመታው ግን ፤ የኢትዮጵያን ሀገራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ በተደራጁ ኃይሎች ሲመራ ብቻ ይሆናል ፡፡ ያ ካልሆነ፤ ትግሉ ግቡን ሊመታ አይችልም ፡፡ የተነጣጠለና የተንጠባጠበ ሕዝባዊ አመፅም ሆነ ያልተቀነባበረ ሀገራዊ ትግል፤ ተልፈስፍሰው ይቀራሉ እንጅ ድልን አያስመዘግቡም ፡፡

የባዕዳኑን አታላይ ዲፕሎማሲ አምኖ መዘናጋት፤ " ያልጠረጠሩ ተመነጥሩ " ለሚለው ተረት፤ መተረቻ መስጠት ነው ፡፡ ዴሞክራሲ ከሌለ ፤ ርዳታ አንሰጥም ( ኖ ዴሞክራሲ፤ ኖ አሲስታንስ " ) ብለው፤ በወቅቱ ተጋግሎ የነበረውን ሕዝባዊ አመፅ፤ በቀዝቃዛ ውሃ እንዴት አድርገው እንዳቀዘቀዙት ፤ ዛሬ ስናስታውሰው ፤ እንደ ዕግር ዕሳት የሚያቃጥል የቁጭት ትዝታችን ሆኖ ቀርቷል፡፡ በሕዝባዊ አመፅ አምባገንኑን ሥርዓት ራሱ አስወግዶ ራሱ- በገዛ እጁ፤ የራሱን ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር እራሱ እስካልመሰረተ ድርስ፤ በባዕዳን በጎ ፈቃድና ርኅራኄ በሀገራችን የዴሞክራሲ አስተዳደር ጮራውን ይፈነጥቃል የሚል ካለ እርሙን ያውጣ ፡፡ ታዲያ አማራጩ ምን ይሁን ? የሚሉ ካሉ፤ መልሱ፤ በራስ ላይ የተማመነ ሕዝባዊ አመፅ ማካሄድ፤ መተኪያ የለውም የሚል መልስ ይሰጣቸዋል ፡፡

ኢትዮጵያ፤ እጅግ ተፈላጊ/ አስፈላጊና ጠቃሚ፤ የሆነች ሀገር ለመሆኗ፤ ማንም የሚያውቀው ነው፡፡ ባላንጣዎቿም ይህንን በመረዳት ነው፤ ሊለቋት የማይፈልጉ፡፡ ትላንት ተገንጥለው የሄዱትም ቢሆኑ፤ ፤ ይኸው ዛሬ ነፃ አወጣናት ያሏትን ክፍለ ሀገር እየለቀቁ በየወሩ፤ ቁጥራቸው በሺህ የሚቆጠረው ወደ ዐባይ ኢትዮጵያ እየጎረፉ ይገኛሉ፡፡ በበርካታ ሺህ የሚቆጠሩትም ወጣቶች በኢትዮጵያ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ውስጥ ገብተው ትምህርታቸውን ይከታተላሉ ፡፡ በውስጣቸው ግን የሻዓብያ ሰላዮች አይኖሩም ማለት የዋህነት ይሆናል፡፡ ወያኔ ይህንን ማድረጉ፤ ለፖለቲካ ስሌቱና ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ መሆኑ ቢታወቅም፤ አርቆ ተመልካቹ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን፤ ዛሬም እንደ ጥንቱ እሰይ ወገኖቼ ! እንኳን ወደ ቤታችሁ መጣችሁ ከማለት በቀር፤ የተለየ ስሜት አላሳያቸውም ፡፡ " እውነትና ንጋት እያደረ ይፈጋል " እንደሚባለው፤ ሀቁ የሚነገርበት ጊዜው በመድረሱ፤ አሁን ራሳቸው ሻዓቢያዎችም ሳይቀሩ፤ እውነቱን አፍጠርጥረው በመናገር ላይ ይገኛሉ ፡፡ የታሪክ ጉዞም፤ ትዝብቱን በሚከተለው ስንኝ ቋጥሮታል ፡፡

ዐይኔ ምን ዐየ እግሬ ደርሶ፤

የሀሰት ልሳን ረክሶ ፤

ዕውነተኛው ታሪክ ተከስቶ፤

የሀቅ ምዕራፍ ተከፍቶ፤

የቀጣፊዎቹ አፍ ተዘግቶ።

ጀሮየም ሰማ እቅጩን

የጥንት የጧቱን፤ ጊዜ የማሽረውን፤

ኢትዮጵያዊነትን !

የፖለቲካ ድርጅቶችና ታጋይ ኃይሎች፤ ከሁሉ አስቅድሞ፤ በዕውነት ላይ ተመስርተው፤ ስለ ዕውነት ቆመው፤ በዓላማቸው ጸንተው፤ ማነታቸውን ለቆሙለት ሕዝብ በገቢር ካስመሰከሩ፤ የሕዝቡን ሙሉ ትብብርና ድጋፍ እንደሚያግኙ ሊያውቁት ይገባል ። ይህንን ካረጋገጡ፤ ለትግላቸው ግብ መምታት ማረጋገጫ ያገኛሉ። ሕዝባዊ ዓላማ አንግቦ የሚታገል ደርጅትም፤ የማታ ማታ አቸናፊ መሆኑ አይቀሬ ነውና !

የክብደቱና የስፋቱ መጠን ይለያይ እንደሁ እንጅ፤ የዓለም ሀገሮች ሁሉ፤ ተዘርዝሮ የማያልቅ፤ የየራሳቸው ችግር አለባቸው። ይህ ችግር ደግሞ ፤ የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚ፤ የገንዝብ ግሽበት፤ የገበያ ምስቅልቅል፤ የማኅበራዊ፤ የሥራ ዕጦት፤ የተፍጥሮ ሀብት ዕጥረት፤ የሃይማኖት አክራሪነት፤ የፀጥታ መደፍረስ፤ የድኅነት፤ የአካባቢ ዐየር ብክለት፤ ( ኢንቫይሮንሜንታል ዲግሬዴሽን ) ወዘተ. ያጠቃላል።

በቴክኒዮሎጅ መስፋፋትና ልዕልና ምክንያት፤ አንዱ ሀገር ከሌላው ጋር የመቀራረቡ ዕድል ሰፊ በመሆኑ ምክንያት፤ የዕውቀት ልውውጥና የሰው ኃይል ዝውውር ቢኖርም እንኳ፤ አንዱ ሀገር በራሱ ችግር የተወጠረ በመሆኑ፤ ስለሌላው ችግር ሊጨነቅ አይችልም ። ይህንን ሃቅ በመመርኮዝ ፤ በማንም ርዳታና ትብብር ሳንተማመንና ሳናተኩር ፤ የራስችንን ችግር ራስችን መፍታት መቻል ይኖርብናል ። በምጽዋዕትና በሌሎች ርጥባን ሀገሩን ያሳደገ ሕዝብ የለም ።

ከዚያ በፊት ግን ፤ የራሳችንን የቤት ሥራ መስራት አለብን። የሀገራን ችግር ቀዳዳው መደፍኑ ቀርቶ፤ እንዲያውም በየጊዜው እየሰፋ መሄዱን አላቆመም ።ስር የሰደደና ዘርፈ-ብዙ ከመሆኑ የተነሳ፤ አንዱን ከሌላው ለይቶ ለማየት ከማይቸልበት ደረጃ እየተደረሰ ነው ። ቅድሚያ ለየትኛው እንደምነሰጠው እንኳን ቅጥ- አምባሩ ጠፍቶብናል ። በሌላ በኩል ግን፤ ችግራችንን ተወጥተን ሀገራችንን አሁን ከግባችበት አዘቅት ልናወጣት የሚያስችለን ሰፊ ዕድልና ኃይል አለን። ይህን ለማለት የምንበቃው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው።

1 ኛ ገና እጥቅም ላይ ያለዋለ፤ ሰፊ የተፈጥሮ ሀብት አለን። በከርሰ-ምድርና ከመሬት በላይ ያለው ድልብ ሀብት ገና አልተነካም ።

2 ኛ. ሰፊና ለም መሬታችን፤ ለዕርሻና፤ ለከበት ግጦሽ፤ ለቤት እንስሳና ለዱር አራዊት እርባታ፤ ሰፋፊ ወንዞቻችንም ለመስኖ

ለኃይል ማምነጫ፤ ለአሳ ሀብት መዛቂያ ይሆኑናል ።

3 ኛ. 90 ሚሊዮን የሚገመተው ሕዝብና የተማረው / የሠለጠነው የሰው ኃይል በአፍሪካ አህጉር በአንደኛ ደረጃ እንደሚገኝ በሰነድ የተደገፉ መረጃዎች ያስረዳሉ ።

4 ኛ ከላይ የተዘረዘሩት ዕውነታዎች ሲጠቃለሉ፤ ለአንድ ሀገር ልማትና ዕድገት የሚሆኑ መስፈርቶች ተሟልተዋል ማለት ይቻላል፡፡

እነርሱም------ሀ. የተፈጥሮ ሀብት፤ ለ.የሠለጠነ ኃይል/ ዕውቀትና ሐ. የሕዝብ ብዛት/ ሀብት ናቸው ።

ሳንታደል በመቅረታችን ብቻ ፤ አንድ ፤እጅግ አስፈላጊ የሆነ ጉዳይ እስካሁን አልተሟላልንም ።ይኸውም፤ ለሕዝብ የቆመ፤ ለሕዝብ የሚያስብና የሚሰራ መንግሥትና የዴሞክራሲ ሥርዓት አለመኖሩ ነው። ይህ ደግሞ በየተፈጥሮ ፀጋ ሳይሆን ሰው ሰራሽ በመሆኑ፤ ሰዎች የራሳቸውን ዕድልና ኑሮ ለማቅናት ከፈለጉ፤ በግድ የሚሆናቸውን የሚበጃቸውን፤ ሥርዓተ መንግሥት መመስረት ይኖርባቸዋል ። እኛም ይህንን ማድረግ ካልቻልን፤ መውቀስ ያልብን ራሳችንን እንጅ፤ ሌላውን አይደለም ። ትላንትም ፤ዛሬም ሆነ ነገ ማድረግ ያለብን፤ያለተቆራረጠ ሕዝባዊ አመፅና ያልትነጣጠለ ሀገራዊ ትግል አካሄዶ፤ ዴሞክራሲያው ሥርዓት መመስረት ነው። ሕዝብ ከተባበረ ደግሞ ይህንን ማድረግ አያስቸግርም ።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች !

Displaying finotehateta_january21_2015.pdf.
Open with